

# ምስክርነቴ

አምላኬ እግዚአብሔር እጅጉን ከበረ፣
ሰማይና ምድርን ብቻውን ፈጠረ ።
አምናለሁ በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ፣
ከአብ በሰረፀ በአጽናኙም መንፈስ።

አማላጅ አንሻም እርሱ ይበቃናል፣
በመስቀል ላይ ሁኖ ፍቅሩን ገልጦልናል።
ወዳጄ ነውና ከሞት ያዳነኝ፣
የዘላለም ሕይወት ፈቅዶ የሰጠኝ።

ጻድቅ በመሆኑ ጽድቁ ያፀደቀን ፣
ፍቅር በመሆኑ ወዶ ያዋደደን።
ብርሃን በመሆኑ ፈጣሪን ያሳየን፣
የዘላለም ሕይወት ክርስቶስ ነው ያለን።

አልገባኝም ነበር የአምላኬ ምስጢሩ፣
ቅዱስ ቃሉን ልኮ በድንግል ማደሩ።
በሥጋ መወለድ አይደለም ለእርሱ ክብሩ፣
ከሞት ሊያድነን መሞት ነበር ፍቅሩ።

ዐይንም አበራ ሙታን ቀሰቀሰ፣
ጎባጣ አቀና ህሙማን ፈወሰ፣
ማዕበልን ገሰፀ ንፋስ አስታገሰ፣
ይህም በደል ሆኖ ጌታ ተከሰሰ።

ጲላጦስም ሰማ የክሱን ወቀሳ፣
እጁንም ታጠበ የለውም አበሳ።
ሕዝቦችን ለማዳን ወዶ ስለመጣ፣
በጲላጦስ ችሎት በመስቀል ተቀጣ።
እጁን ቸነከሩት እግሩን ቸነከሩት
ውሃ ጠማኝ ባለ ሆምጣጤ አጠጡት።
ስቃዩ ቢበዛ ጮኸ የኔ ጌታ፣
ራሱም ዘንበል አለ ሞተ በጎልጎታ።

ሰቀሉት ገደሉት ንጹህ ደም ፈሰሰ፣
መድኃኒት ነውና አማኝ ተፈወሰ።
ከዚያም በመንፈሱ ወረደ ሲኦል ፣
በመቃብር ላሉት ሰበከ ወንጌል።

ሞቶ ግን አልቀረም ተነሣ ያ ጌታ፣
የሰማይ መላእክት ዘመሩ በርካታ
እህቶቹ ሄዱ ሽቱ ሊቀቡት፣
መቃብሩ ባዶ ሆኖ አገኙት።

ስለዚህም ፈሩ ሮጡ ወደ ቤት ፣
ቀደመና ጌታ ማርያምን ጠራት፣
ረቡኒ ! አለች ድምፁን አወቀች፣
ፈጥናም ከእግሩ ስር መሬት ወደቀች።

ከገሊላ ይምጡ እዚያ እገኛለሁ፣
ደቀ መዛሙርቴን አነጋግራለሁ፡
ሁሉንም አገኘ መከረዘከረ፣
ለአርባ ቀናትም አብሮአቸው ነበረ።

አባት እንደሌለው እርሱ መቼ ተዋቸው፣
ክብርና ጸጋውን መንፈሱን ሰጣቸው።
ጥቂት ተራመደ ከፊት ለፊታቸው፣
ብድግ ብሎ ወጣ አድማስ ከለላቸው።
ዓለም ሳይፈጠር ቀድሞ እንደነበረ ፣
በአባቱ ዙፋን ዳግመኛ ከበረ።
መኖሪያ የሚሆን ሥፍራ አዘጋጅቶ፣
ጌታ ይመለሳል ይወስደናል መጥቶ።

አጀቡ ብዙ ነው ሲወርድ ከሰማይ፣
ሺህ አመት ይነግሳል በዚህ ምድር ላይ።
እኛም ወዳጆቹ እንነጠቃለን፣
በኢየሱስ መንግስት አገር እንገዛለን።

ይህንን ሰምቼ አመንኩኝ በጌታ፣
ታሪኬም ታደሰ አገኘሁ እርካታ።
መሐሪ ነው እርሱ ደሙ ይቀድሳል፣
በጠባቢቷ በር ከገነት ያደርሳል።

በገና እንስቶ ቅኔ መደርደር ፣
የተለመደ ነው ለእግዚአብሔር መመስከር።

..........................................................................................

ከጆቢር ሄይኢ.